# ማስጠንቀቂያ፦ ኩል (KOHL) እርሳስ (ሊድ) ሊኖረው ይችላል

## እርሳስ (ሊድ) ለምንድን ነው አደገኛ የሆነው?

እርሳስ (ሊድ) ወደ ሰዎች የውስጥ አካል ከገባ ጉዳት ሊያስከትል የሚችል መርዛማ ብረት ነው። እርሳስ (ሊድ) መደበኛ የአዕምሮ እድገትን ሊጎዳ የሚችል በመሆኑ **ወጣት ልጆች እና በእርግዝና ላይ ያሉ ሴቶች** ለዚህ አደጋ ተጋላጭ ናቸው።

## እርሳስ (ሊድ) በኩል፣ ካጃል፣ ሱርማ፣ እና ሶርሜ ውስጥ

**ኩል፣ ካጃል፣ ሱርማ፣ ወይም ሶርሜ ተብሎ የሚታወቀው ጥቁር የዓይን ዱቄት እርሳስ (ሊድ) ሊኖረው ይችላል።** ይህ ዱቄት ዓይን ወይም አፍ ውስጥ ከገባ ለእርሳስ (ሊድ) ሊጋለጡ ይችላሉ።

## ስለዚህ ይህን ለመከላከል ምን ማድረግ ይችላሉ?

- አንዳንድ ምርቶችን ከነኩ በኋላ እጆችዎን ይታጠቡ።
- **የዕቃ መያዣዎችን** ከሕጻናት አርቀው ያስቀምጡ።
- **በተቻለ መጠን** ከእርሳስ (ሊድ) ነጻ የሆኑ አማራጮችን ይጠቀሙ።
- **የደም እርሳስ (ሊድ) ምርመራ** እንዲያደርግልዎ ሐኪምዎ ይጠይቁ።
- **ምርትዎን ይሞክሩ** ስላሉ አማራጮች በሊድላይን 503-988-4000 ላይ ስልክ በመደወል።

## ጥያቄዎች?

www.leadline.org ይጎብኙ ወይም 503-988-4000 ላይ ስልክ ይደውሉ

WASHINGTON COUNTY OREGON | Oregon Health Authority | Multnomah County Health Department







## ምን ዓይነት ምርቶች ናቸው እርሳስ (ሊድ) የሚኖራቸው?

ለኦሬጎንያንስ (Oregonians) ዋነኛው የተጋላጭነት አደጋ የሚኖረው እርሳስ (ሊድ) ያለበት በአሮጌ ቤቶች ውስጥ የሚኖር ቀለም ቢሆንም እርሳስ (ሊድ) በተለያዩ ምርቶች ውስጥ ወይም በየዕለቱ በምንጠቀምባቸው ቁሳቁሶች ውስጥ ሊገኝ ይችላል።

ማህበረሰቡ ከዚህ እንደሚከተሉት ባሉ ባህላዊ ምርቶች ውስጥ ሊኖሩ በሚችሉ እርሳስ (ሊድ) ምክንያት ስላለ የተጋላጭነት የተለየ አደጋ ግንዛቤ ሊኖረው ይገባል፦

- እርድ
- ኮስሞቲክስ
- ቀለም ያላቸው ዱቄቶች
- የጤና መድሃኒቶች
- አሸንክታብ/ክታብ
- የሸክላ ዕቃዎች

አንድ ዕቃ ወይም ምርት እርሳስ (ሊድ) ሊኖረው ይችላል የሚል ስጋት ካደረብዎ **ለምርመራ** 503-988-4000 **ላይ ስልክ ይደውሉ።**

በእርሳስ (ሊድ) የመመረዝ ምልክቶች በቀላሉ የሚታዩ አይደሉም። በእርሳስ (ሊድ) የተመረዙ ሕጻናት ወይም አዋቂ ሰዎች ሕመም ያለባቸው ላይመስሉ ወይም ሕመም ላይሰማቸው ይችላል።



እርስዎ ወይም የቤተሰብዎ አባላት በእርሳስ (ሊድ) የመመረዝ ተጋላጭነት ካለባችሁ **ሐኪማችሁ በደማችሁ ውስጥ እርሳስ (ሊድ) ስለመሆኑ ምርመራ እንዲያደርግላችሁ ይጠይቁ።**

## ጥያቄዎች?

www.leadline.org ይጎብኙ ወይም
503-988-4000 ላይ ስልክ ይደውሉ

WASHINGTON COUNTY OREGON

Oregon Health Authority

Multnomah County Health Department